ዛሬ እንኳን እንሳቅ!

ፈገግታ የሚጭሩ ቀልዶች!

በቶዱስ-ሃብት በላቸው

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

<<ሳቅ ሆርሞኖችን ያነቃቃል፤ ያሳድጋል፤ ውጥረትና ጭንቀትን ይቀንሳል፤ ሰውነታችንን ያፍታታል፤ ውስጣዊ አካላችን የተቀላጠፈና የተስተካከለ ስራውን እንዲሰራ ይረዳል። በተለይም ከልባችን የምስቀው ሳቅ የመተንፈሻ አካላችንን፤ ትከሻችንን፤ ጡንቻዎቻችንን ከማዝናናቱ በተጨማሪ ልባችን ባግባቡ ስራውን እንዲያከናውን ያግዛል።

ሳቅ ቁጣን፤ ንዴትና የመሳሰሉትን አሉታዊ ስሜቶች ያስወግዳል። ከዚህም በተጨማሪ ሳቅ ማሕበራዊ ጥቅምም አለው። ሳቂታነት ከሰዎች ጋር በቀላሉ እንድንግባባ ከማድረጉ በተጨማሪ ሰዎች ስለኛ መልካም ስሜት እንዲያድርባቸው ያደርጋል። እርሶ ሲስቁም ሌላውን ፈገግ እንዲል ይጋብዙታል።>>

ታዋቂዋ የስነ-ልቦና ምሁር ኤልሳቤጥ ስኮት

Kedus-habt Belachew
efjakhb@yahoo.com

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የመጽሃፏ መታሰቢያነት



ይቺ ትንሽ መፅሃፍ መታሰቢያነቷ በኢትዮጵያ ውስጥ የፕሬስ ነፃነት እንዲከበር መስዋዕትነት ለከፈሉና እየከፈሉ ላሉት የኢትዩጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች በሙሉ፤ በተለይም የ1997 ዓ.ም ምርጫን ተከትሎ እውነትን ለሕዝብ ማሳወቃቸው ከወንጀል ተቆጥሮባቸው ለእስር ተዳርገውና ሁለት አመታት በስቃይ አሳልፈው ከተፈቱ በኋላ፤ በአምባገነኑ የወያኔ/ኢሕአደግ መንግስት ሰብዓዊ መብታቸው ተጥሶ በምንም አይነት የጋዜጠኝነት የስራ መስክ ላይ እንዳይሰማሩ ታግደው ለሚገኙት ለሙያ ባልደረቦቼና ለቅርብ ወዳጆቼ ለጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፤ ለባለቤቱ ለጋዜጠኛ ሰርካለም ፋሲል፤ እንዲሁም እስር ቤት ውስጥ ሳሉ ለተወለደው ታሪከኛ ልጃቸው ለሕፃን ናፍቆት እስክንድር፤ ..... በአንባቢያን ዘንድ እጅግ ተወዳጅ ለነበረችው ኢትኦጵ መፅሄትና ጋዜጣ፤ አሳታሚ ለነበረው ለምግባረ-ሰናዩ የሙያ አጋሬ ለጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና ትሁንልኝ፡፡ (ቅዱስ-ሃብት በላቸው)

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ማውጫ

ገጽ

ሶስት ብርጭቆ መጠጥ 1
አንጎራጓሪዋ ሚስት 2
የወንዶች ነገር 3
የሰካራም ነገር 4
አግአዚና የትራፊክ ፖሊስ 5
የዲቪ ነገር 6
ምርጫና የአውሮፓ ክስቦች ዋንጫ..........................7
ምክር ከአገሩ ላልወጣ ሰው..................................8
ለቅሶና ምርጫ... .9
ቅጽል ስም...11
ልጆች ለእግዚአብሔር ከፃፉቸው ደብዳቤዎች 12
የፍተሻ ስራ...13
የእውነተኛው ፈረስ ስም 14
የማሙሽ ነገር... 15
ፕሬዚዳንታችን.. 16
መብራቱ ገ/ህይወት 18
አገራችንና የኑሮ ውድነት 19
የልጅ ነገር 21
አግአዚና ፍቅር 22
ቅዱስ ገብርዔል ተከተለኝ 23
ኣውቶቡስ ጠባቂዎቹ 24
የመንግስቱ ኃ/ማሪያምና የመለስ ዜናዊ ሚስቶች የስልክ
ወግ 25
የቀብር ፈቃድ 30
ዳኛና ተከሳሽ 31

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ማውጫ

ፍቅርና ገንዘብ 31
የመረረው የአበሻ ልጅ 32
አሜሪካና ሰዓት አቆጣጠር 33
የባል፣ኑዛዜ 34
አባ፣ጳውሎስና ልደታ... 35
እስኪርቢቶ የዋጠው ልጅ 37
ቦክሰኛና ጋዜጠኛ 37
ተወደድኩ ባይ 38
ምግብ ቤት 38
የባልና ሚስት ነገር 39
መቶ ብርና የወያኔ ጠላትነት 40
የነጋዴ ልጅ 41
የመጠጥ ነገር 42
የመዳሻ ሰዓት 43
የአውቶቡሱ ሾፌር 44
ሰብዓዊ መብት 45

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ሶስት ብርጭቆ መጠጥ

አንድ ሰውዬ ሁልጊዜ ወደ ቡና ቤት ጎራ ሲል አንድ አይነት መጠጥ በሶስት የተለያዩ ብርጭቆዎች በማዘዝ ፊት ለፊቱ ደርድሮ በየተራ ከሶስቱም እየተጎነጨ ነው የሚጠጣው። ታዲያ ይህ ከሰው ለየት ያለ ባሕሪው የሚያስገርመው የመጠጥ ቤቱ አስተናጋጅ አንድ ቀን «ይቅርታ ወንድሜ! .... ሁል ጊዜ አንድ አይነት መጠጥ በሶስት ብርጭቆ እያዘዝከኝ ሁሉንም የምትጠጣው ግን አንተው ነህ፤ ከዚህ ሁሉ አንዱን ጠጥተህ ስትጨርስ ሌላውን ባመጣልህ አይሻልም?» ሲል ይጠይቀዋል።

ሰውየውም *«የለም! የለም! አየህ! ይህ ትልቅ ምክኒያት አለው፤ አንዱ ብርጭቆ የኔ ድርሻ ሲሆን ሁለቱ ግን ለስራ ፊልድ የሄዱ በጣም የምወዳቸው ጓደኞቼ ድርሻ ነው:: ስለዚህ እነሱን ለማስታወስ ስል ነው በሶስት ብርጭቆ አዝዤ የምጠጣው»* ሲል ይመልስለታል።

ታዲያ አንድ ቀን ሰውየው ያለወትሮው- ሁለት ብርጭቆ መጠጥ ብቻ ቢያዘው፤ አስተናጋጁ ግራ በመጋባት *«ውይ!!፡ ዛሬ ምነው ሁለት ብቻ አዘዝከኝ?! አንዱ ጉዋደኛህ ሞተ እንዴ?'* ሲል ይጠይቀዋል። ...

ሰውየውም *«የለም! የለም!፦ ሁለቱም ኸረ ደህና ናቸው!! እኔ መጠጥ ስላቆምኩ፤ የራሴን ድርሻ ቀንሼ ነው»* ብሎት እርፍ!!

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

አንጎራጓሪዋ ሚስት

ሴትዮዋ ሲፈጥራቸው ድምፃቸው ባያምርም ሁል ጊዜ መዝፈን፤ ማንጎራጎር በጣም ይወዳሉ። የሚገርመው ነገር ታድያ ብዙ ጊዜ ማንጎራጎር ሲጀምሩ ባለቤታቸው ከቤት በመውጣት ደጅ ላይ ይቆማሉ። ይህም ነገር ብዙ ጊዜ መደጋገሙ "እትዬን" ግራ ቢያጋባቸው አንድ ቀን ባለቤታቸውን *..«አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ.....አረ ለመሆኑ ሁል ጊዜ እኔ መዝፈን ስጀምር ለምንድነው ወደ ወጭ እየወጣህ የምትቆመው?»* ሲሉ ይጠይቋቸዋል።

በዚህ ጊዜ ባልየው መለስ አድርገው *«ምን ላድርግ ብለሽ ነው? ...ጎረቤቶቻችን ድምፅሽን ሲሰሙ የምደበድብሽ እንዳይመስላቸው ብዬ ፈርቼ ነው.!!...»* በማለት የድምጻቸውን አስቀያሚነት በዘዴ ነገሩዋቸው ይባላል።

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የወንዶች ነገር

አባትና የደረሰች ሴት ልጁ እየተጨዋወቱ ሳለ ልጅ በመሃል *«አባዬ ! ትናንትና ከኔ ጋር ያየኸው ልጅ እኮ እጮኛዬ ነው፤ ደስ አይልም?»* ብላ አባቷን ትጠይቀዋለች።

<u>አባት፦</u> *«ጥሩ ነው፤ ጨዋ ሰው ይመስላል .... ለመሆኑ ደህና ገንዘብ አለው?»*

<u>ልጅ፦</u> *«በጣም ይገርማል!! ... እንዲያው ወንዶች ስትባሉ በቃ ባህሪያችሁ አንድ ነው ማለት ነው?!! ... እርሱም ሁል ጊዜ ስላንተ የሚጠይቀኝ አባትሽ ምን ያህል ገንዘብ አለው እያለ ነው!!»*

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የሰካራም ነገር



አንዲት ያለአቅሟ ጠጥታ በመጠጥ ድንብዝ ያለች ሰካራም ፖሊስ ጣቢያ ስልክ ትደውልና *«እረ የመኪናዬ እቃ በሙሉ ተዘርፏልና ድረሱልኝ!»* ስትል ታመለክታለች።

ተረኛው ፖሊስም የተሰረቀባትን እቃ በቅድሚያ እንድታስመዘግብ ሲጠይቃት «መሪው፡ የእጅ ፍሬኑ፤ ማርሹ፤ ፍሪሲዮኑ፤ የእግር ፍሬንና ነዳጅ መስጫው ሁሉ እንደሌለ ተናገረችና ስልኩን ዘጋችው።

ሆኖም ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ይቺው ሴትዬ ወደ ፖሊስ ጣቢያው መልሳ ትደውልና ለፖሊሱ *"ይቅርታ ጌታዬ በስህተት በመኪናዬ የኋላ በር ገብቼ ነው እንጂ ሁሉም ነገር አለና ....በቃ ተውት!'* አለቻቸው::

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

አግአዚና የትራፊክ ፖሊስ

(ይህ ነገር በትክክል የደረሰ እንደሆነ ወዳጆቼ በወቅቱ አጫውተውኛል)

አንድ የታክሲ ሹፌር አዲስ አበባ ውስጥ ትርፍ ሰው ጭኖ ሲንዝ የትራፊክ ፖሊስ ያስቆመውና ሹፌሩን ከመኪናው አስወርዶ ሊቀጣው እየተጨቃጨቁ ሳለ በአካባቢው የነበረ አንድ የአግአዚ ወታደር ሰምቶ ወደ እነርሱ ይሄዳል፡፡

«ምን ሆናችሁ ነው "የምትጨቃጨቁት?»



ትራፊክ ፖሊሱም *«ትርፍ ሰው ጭኖ ሲሄድ አግኝቼው ነው»* በማለት ይመልስለታል

አግአዚውም ግራ በመጋባት ወደ ሾፌሩ ዞሮ *«ዋይ..!.. ስመሆኑ መኪናው የማን ነው?»* ሲል ይጠይቀዋል

ሾፌሩም በዚህ ጊዜ መንጃ ፈቃዱንና የመኪና ባለቤትነት ሊብሬውን አውጥቶ ያሳየዋል፤

በዚህ ጊዜ አግአዚው በጣም ይናደድና ወደ ትራፊክ ፖሊሱ ዞሮ *«ኣታ! ወዲ አድጊ !! በራሱ መኪና እንደ ፈለገ ቢጭንበት አንተ ምን አገባህ?!!»* በማለት የትራፊክ ፖሊሱን ሰድቦና ደብድቦ አባረረው፡፡

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የዲቪ ነገር

ልጅቷ ዲቪ ይደርሳትና ወደ አሜሪካ ለመሄድ ስትዘጋጅ ለአባቷ አንድ *«አባዬ ! አሜሪካ እንደገባሁ እንደምንም ብዬ አንድ ታክሲ የምትሆን ሚኒባስ ገዝቼ እልክልሃለሁ እሺ!»* በማለት ቃል ትገባላቸዋለች።

ሆኖም አሜሪካ ከገባች አመታት ቢቆጠሩም እንዳሰበችው ሳይሆን ይቀርና፤ እንዲያውም ካገኘችው ወንድ ጋር ስትዘልና ስትቀብጥ ሳታስበው ፀንሳ ወንድ ልጅ ትወልዳለች።

ታዲያ የወለደችውን ልጅ አሜሪካ ውስጥ ያለአባት ማሳደግ ቢከብዳት አገር ቤት የሚገኙት አባቷ ያሳድጉላት ዘንድ አሳፍራ ትልከዋለች። ይህም ግራ ያጋባቸው አባት ወዲያው ለልጃቸው ስልክ ደውለው *«ምነው ልጄ?! እኔ ከዛሬ ነገ ሚኒባስ ትልኪልኛለሽ ብዬ ስጠብቅ፤ ምነው ከታክሲው በፊት ወያላውን አስቀድመሽ ላክሺልኝ?»* አሏት ይባላል።

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ምርጫና የአውሮፓ ክለቦች ዋንጫ

የምርጫ 97 ሰሞን አንድ ወጣት የአውሮፓ ክለቦች እግር ኳስ ጨዋታ ሲከታተል ቆይቶ የሚደግፈው ቡድን ስላሸነፈ ደስ ብሎት እየጨፈረ ወደቤቱ በመሄድ ላይ ሳለ አንድ የአግአዚ ወታደር መንገድ ላይ ይይዘውና *«አታ አድጊ!.. ምን ስላገኘህ ነው የምትጨፍረው?.... የቅንጅት ደጋፊ ነህ አይደል?.አውጣ!!.»*.ሲል ያፈጥበታል።

በአጋጣሚው የተደናገጠው ወጣትም እየተርበተበተ... *«የአርሴናል.ነኝ!!.. አርሴናል ስላሸነፈ ነው!!»* ብሎ በፍርሃት እየተርበደበደ ሲመልስለት የአግአዚው ወታደር በሰደፉ አንዴ ያቀምሰውና...*«ያሸነፈው ኢሕአዴግ እንደሆነ ልክ ስናስገባህ ታምናለህ!!»* ብሎት እያገላበጠ ይዞት ሄደ ይባላል።

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

«ምክር ከሃገሩ ላልወጣ ሰው»

«የየሰማ ላልሰማ!!..ይህንን ጉድ አውቀህ ግባበት!!

(የአራዳ ልጅ ምክር ከውጭ አገር)

«በጥሩ ኑሮ ላይ ካላችሁ ማለትም ስራ ትንሽም የምትሰሩ ከሆነ፡ ከሃገር አትውጡ አደራ!! በተለይ ደግሞ የቢሮ ስራ የምትሰሩ ከሆነማ ስደት በሃሳባችሁ አይምጣ። ስራ አጥ ወይም አደገኛ ቦዘኔ ተብለህ ተፈርጀህ ከሆነ ግን ትጠቀማለህ፤ ለትምህርት ከሆነም እሰየሁ!! እዚህ እኔ የምገኝበት ሃገር ሰርተህ ለመኖር የፈረስ ገላ በየቀኑ በደንብ ማጠብ፤ እንዲሁም የፈረሱን ጥርስ በአኩአፍሬሽ ወተት እስኪመስል መቦረሽ ይጠበቅብሃል።

ወደድክም ጠላህ ያለው ክፍት የስራ ቦታ ደግሞ ይህ በመሆኑ ለመኖር ስትል ግዴታ ትሰራለህ። ታዲያ የፈረሱን ገላ ከማጠብ ይበልጥ በጣም የሚያናድድህና የሚያስጠላህ ስራ ቢኖር የፈረሱን ጥርስ ወተት እስኪመስል በጥርስ ሳሙና መቦረሽ ነው። አንዳንዴ ለመሸወድ አስበህ ጥርሱን ነካ ነካ አድርገህ በደንብ ሳታጥበው ብትተወው እንኳዋን ፈረሱ የዋዛ እንዳይመስልህ። ....ባለቤቱ ሲመጣ በቆሻሻ ጥርሱ ስቆ ያስፎግርሃል።



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ለቅሶና ምርጫ

በግንቦት 1997ዓ.ም ምርጫ በሕዝብ ድምፅ መሸነፉን የተረዳው መለስ ዜናዊ በምርጫው ማግስት እራሱ በልዩ ትዕዛዝ የሚያዘውን ጨፍጫፊ የአግአዚ ጦር አዲስ አበባ ውስጥ በመበተን ማንኛውንም ሰላማዊ ሰልፍ፤ ስብሰባ፤ ...ወዘተ፤ ማድረግ ክልክል እንደሆነ የሚደነግግ አዋጅ በአንድ ቀን አውጥቶ እንደነበር ይታወሳል። ይህን ተከትሎም ሰዎች በተለይም ደግሞ አዲስ አበባ ውስጥ ወጣቶች ሰፈራቸው ውስጥም ቢሆን ሰብሰብ ብለው ከታዩ እንዲበተኑ ይነገራችዋል፤ እምቢ ካሉም የአግአዚ ወታደሮች የጥይት ሰለባ ይሆናሉ፤ ሆነዋልም።

ታድያ አንድ መንደር ውስጥ አንድ ትልቅ ሰው ሞቱና የአካባቢው ሰው ተሰባስቦና ድንኳኑን ግጥም አድርጎ ....ስለ ምርጫውና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ስላገኙት ውጤት በከፍተኛ የድል መንፈስ ተመስጠው እየተጨዋወቱ ሳለ፤ ወትሮም ተፈጥሮ ባኮሠሠው ፊቱ ላይ በምርጫው ወያኔ የደረሰበት ሽንፈት ፊቱን አመድ ያስመሰለው የሕወሃት ካድሬ ድንገት ድንኳኑ ውስጥ ዘው አለ....ህዝቡም ከአንድ ሙሉ ጀንያ ጤፍ እንደ ወደቀች ቅንጣት ፍሬ ጉዳይ ሳይሰጠው ጨዋታውን ሲቀጥል.....ይሄው ካድሬ ብግን ብሎ ➡

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ከመቀመጫው በመነሳት.....«..ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ መሰብሰብና ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ ከልክለዋል ....እናንተ እዚህ ተሰብስባችሁ አዋጁን የሚጻረር ተግባር እየፈጸማችሁ ነውና አሁኑኑ እንድትበተኑ!!.....»ብሎ ማስጠንቀቂያ አከል ትዕዛዝ ሲናገር .....አፋቸውን በነጠላ የሸፈኑ እናቶች ቀበል አድርገው ፈራ ተባ በሚል መንፈስ .«ምነው ወንድም?!......ለቅሶ እኮ ነው!!..ኡኡቴ!!......ምነው አንተ...? በደጉ ዘመን ልጅህ ብትሞት እስከ አርባ ቀን ቤትህ ደጃፍ ተቀምጠን አልከረምንም እንዴ?...ምነው አንተ አዋጁን ከተናገሩት ሰው ባስከው?!...ሰው ሲሞት ለቅሶ አትቀመጡ ትለናለህ?» ብለው ቢመልሱለት....

«ትሰሙኛላችሁ?!! ....እንግዲያውማ አዋጁ እስኪነሳ መሞትም በጥብቅ የተከለከለ ነው!!..»ብሎ እርፍ.... (ከኢትኦጵ)

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ቅፅል ስም

መቼስ በሃገራችን ለሰው ልጅ አይደለም ለከብትም ቢሆን ከባሕሪይውና ከተግባሩ ጋር የተያያዘ ቅፅል ስም ማውጣት የተለመደ ነገር ነው። ታዲያ እንደዋዛ የወጡ አንዳንድ ቅፅል ስሞች ከእውነተኛው ስም በበለጠ ለተሰየመው ሰው መጠሪያና መታወቂያ ሆነው እስከ እድሜ ልክ ያገለግላሉ።

ታዲያ እኔም ባደግኩበት ሰፈር የምንገኝ ልጆች በሙሉ ማለት እችላለሁ ሁላችንም ቅፅል ስም ነበረን። ታዲያ ከመሃከላችን አንደኛው እጅግ አስደናቂ የሆነ ማንነቱን በትክክል የሚገልፅ ቅፅል ስም ባንድ ጓደኛችን ወጥቶለት ነበር።

ይኸው ልጅ በመንደራችን ውስጥ የሚገኙ ዶሮዎችን አሳዶ በመያዝ እየሸጠ ፓስቲ በመብላት የታወቀ ነበር። ለዚህ ለተካነበት ተግባሩ የወጣለት ቅፅል ስም ታዲያ የአንዲት የሃገራችን ታዋቂ ድምፃዊ እውነተኛ ስም ነበር። ……«ኩኩ ሰብስቤ» …….. (ዶሮ ሰብሳቢ) በነገራችን ላይ በዚህ አጋጣሚ ለድምፃዊ ኩኩ ሰብስቤ ተሰምተው የማይሰለቹ ድንቅ የሙዚቃ ስራዎች ያለኝን አድናቆትና ፍቅር ለመግለፅ እሻለሁ።

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ልጆች ለእግዚአብሄር ከጻፉአቸው ደብዳቤዎች

የተወደድከው እግዚአብሄር ሆይ!! ጉንጭህን ስሞ በሰላሳ ብር

አሳልፎ የሸጠህ ይሁዳ ምን አይነት ደደብ ሰው ቢሆን ነው? እንኳን አንተ የኛ ጌታ አይደለህም፤ እኛ ቤት ያለችው ሰራተኛችን እንኳን በወር ደሞዟ ሰማንያ ብር ነው።

.......//............

***የተወደድከው እግዚአብሄር ስሜ ጨቡዴ ነው: የትምህርት ቤት ጓደኞቼ በስሜ ሁል ጊዜ ያሾፉብኛል። ስለዚህ እኔ ስምን መልዓክ ነው የሚያወጣው ሲባል ስለሰማሁ የኔን ስም ያወጣውን መልአክ አደራ ቅጣልኝ። <u>ጨቡዴ ነኝ</u>

..........................//..........................

*** እግዚአብሄር አምላክ ሆይ! .አባዬ ሁልጊዜ አሞኛል እያለ አልጋው ላይ ተኝቶ ያቃስታል፤ ታዲያ አንዳንዴ ወደ ውጭ ወጣ ሲል መንገድ ላይ ያገኙት ጓደኞቹ «ደህና ነህ ወይ?» ብለው ሲጠይቁት ግን "**እግዚአብሄር ይመስገን በጣም ደህና ነኝ**" ይላል አይገርምህም? እነሱንስ እሺ ይሸውድ! ..... አንተን ግን እንዴት ይዋሽሃል?

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የፍተሻ ሰራተኛ

አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኝ ድርጅት በሩ ላይ የፍተሻ ስራ የሚያከናውኑ ሰራተኞችን ለመቅጠር ማስታወቂያ አውጥቶ፤ በርካታ ስራ ፈላጊዎች ለመቀጠር እየሄዱ የድርጅቱ ሃላፊ ሁሉንም በየተራ ቃለ-ምልልስ እያደረገ ነው።

ቀጣሪ፦ *«በፍተሻ ስራ ካሁን ቀደም የስራ ልምድ አለህ?»*
ተቀጣሪ፤- «አዎን ጌታዬ! .... የ10 ዓመት ልምድ አለኝ።»
ቀጣሪ፤- *«ለመሆኑ የት ነበር ትሰራ የነበረው?»*

ተቀጣሪ፤- «አንበሳ የከተማ አውቶቡስ ላይ!»

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የእውነተኛው ፈረስ ስም

ከጥንት ጀምሮ የነበሩ የሃገራችን ነገስታትና ታዋቂ የጦር መሪዎች የሚጠሩበት የፈረስ ስም እንደነበራቸው ይታወቃል። እንደ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል የአፄ ቴዎድሮስ የፈረስ ስም ***«አባ ታጠቅ»*** ፤ የአፄ ዮሃንስ ***«አባ በዝብዝ»*** የአፄ ምኒልክ ***«አባ ዳኘው»*** ፤ የልጅ እያሱ ***«አባ ጤና»***፤ የአፄ ኃይለ ስላሴ ***«አባ-ጠቅል»***፤ የደጃች ባልቻ፤ ***«አባ ነፍሶ»*** ..ወዘተ እየተባሉ ይጠሩ ነበር።

ታድያ ለቀድሞዎቹ ብቻ ሳይሆን ለዘመኑም የሃገራችን መሪዎች ብዙም ባይታወቅም ሕዝባችን የፈረስ ስም አውጥቶላቸዋል....ለፐ/ት መንግስቱ ኃ/ማርያም ***«አባ በለው»*** ሲሆን የመለስ ዜናዊ ማን ይመስላችኋል?

«አባ ዱላ»!!!............ሲያሻው መከላከያ ሚ/ር፤ ሌላ ጊዜ የኦሮሚያ ክልል ፐ/ት፤ የኦህዴድ ሊቀ መንበር፤ አንዴ ጀነራል ሌላ ጊዜ ተራ ሰው የሚያደርገው የወያኔ ቡችላ ***«አባ-ዱላ ገመዳ »*** እውነተኛ የመለስ ፈረስ አይደለም ትላላቹህ? ..በነገራችን ላይ በኦሮሞ ሕዝብ ስም የሚያጭበረብረው የዛሬው አባ ዱላ ትክክለኛ ስሙ <u>አስር አለቃ ምናሴ ወ/ጊዮርጊስ</u> ሲሆን በሻዕቢያ ተማርኮ ከአመታት የእስር ቤት እንግልት በኋላ ለወያኔ ተላልፎ የተሰጠ የደርግ ምርኮኛ ወታደር ነው።

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የማሙሽ ነገር

እናት…«*ማሙሸዬ !…ነግሬሃለሁ ከዛሬ ጀምሮ ያገኘኸውን ሁሉ ዝም ብለህ አትብላ እሺ?»*

ልጅ….«እሺ እማዬ!… ግን ለምንድነው እንዲህ ያልሽኝ?»

እናት…«*ያገኘኸውን ከበላህ ሆድህ ይቆዘርና ያምሃል።»*

ከቀናት በኋላ አንዲት ነፍሰ ጡር ሴት እነ ማሙሽ ቤት በእንግድነት ትመጣለች። የሴትዮዋን ሆድ ትልቅ መሆን ያስተዋለው ማሙሽም ወደርሷ ጠጋ ብሎ…*« አውቄብሻለሁ! አንቺ !….ሆድሽ እንዲህ የተነፋው ያገኘሽውን እየበላሽ ነው አይደል?»* አላት ይባላል።

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ፕሬዚዳንታችን

መለስ ዜናዊ ከሃገር ውጭ ሳለ አንድ ከወያኔ ባለስልጣናት ጋር ካለው ቀረቤታ የተነሳ ካለ ቀጠሮ የሚመጣ የውጭ ሃገር እንግዳ ወደ ሃገር ቤት ይመጣና ቤተ መንግስት ሲገባ ፕ/ት (የመቶ አለቃ) ግርማን ያገኝና ***«መለስ የት ሄደ?»*** ሲል ይጠይቃል።

መቶ አለቃም ***«እንግሊዝ ሃገር ለስብሰባ ሄደዋል»*** ሲሉ ይመልሳሉ።

«በረከትስ የት ሄደ?»

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

መቶ አለቃ.....«እርሱም ለስብሰባ ፈረንሳይ ሄደዋል።»

«ስዩም መስፍንስ የት ሄደ።»

መቶ አለቃም...«እርሱም ለአስቸኳይ ጉዳይ ወደ ሱማሊያ ሄደዋል።» ብለው ወንበራቸው ላይ እንደተወዘፉ ሲመልሱለት በመገረም *«እነርሱ ሁሉ ሄደው እርሶ ታድያ እዚህ ምን ያደርጋሉ?»* ብሎ ቢጠይቃቸው የወያኔ ትልቁ አሻንጉሊት የሚባሉት አዛውንቱ ፕሬዚዳንት (መቶ አለቃ) ግርማ መለስ አድርገው *« አዩ ልጄ! የኔ ስራ እኮ እነርሱ እስኪመጡ ቤት መጠበቅ ነው።»* አሉት ይባላል።



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

«መብራቱ ገብረ-ሕይወት»

ከታላላቅ የወያኔ ባለሟሎች አንዱ የሆነው በረከት ስምኦን እናት አባቱ መጀመርያ ያወጡለት ስም *«መብራቱ ገብረ-ሕይወት»* መሆኑን ስንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? የዛሬን አያድርገውና የሪፖርተር ጋዜጣ ዋና አዘጋጅና ባለቤት የሆነው የቀድሞ የወያኔ ታጋይ አማረ አረጋዊ የሕወሃት ባለስልጣናት በግንቦት 1997 ዓ.ም ምርጫ በህዝብ ድምፅ ከመዘረራቸው በፊት *«ኢህአዴግ ከየት ወዴት?»*..በሚል ርዕስ «መብራቱ ገብረ-ሕይወት» በሚል የብዕር ስም የወያኔን ገበና በተከታታይ ለረጅም ጊዜ ሲያስነብበን ነበር።

ወደተነሳሁበት ርዕሰ ጉዳይ ልመለስ። የኤሌክትሪክ ሃይል ከደቡብ ተስቦ ወሎንና ሌሎች አካባቢዎችን አቋርጦ ትግራይን እንዳደመቀ ብዙዎቻችን የምናውቀው ሃቅ ይመስለኛል። በዚህም የወሎ ህዝብ እየተበሳጨ ሳለ በረከት ስምኦን ወደ ወሎ በመሄድ የምረጡኝ ቅስቀሳውን ይጀምራል። በዚህ ጊዜ የወሎ ህዝብ ምን እንዳለው ልንገራችሁ.....«*አይ ! አንተም እንደመብራቱ እለፈን*»

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ሃገራችንና የኑሮ ውድነት

ልጅ ከውጭ አገር ለእናቱ ገንዘብ ልኮ የስልክ ውይይት ላይ ነው

ልጅ፤-*«እማዬ ደህና ነሽ?....*

እናት: ደህና! ደህና! ልጄ!!...እግዜር አንተን ብቻ ይጠብቅልኝ!! አንተስ ግን እንዴት ነህ?

ልጅ፤- *ደህና ነኝ እማይዬ! ... ለመሆኑ የላኩልሽ ዶላር ደረሰሽ?»*

እናት፦አዎን ልጄ ! እግዜር ይስጥልኝ! የሞላ እንጀራ ይስጥህ!

ልጅ : *«አሜን!አሜን! እማዬ!! ላንቺ ያልሆንኩ ለማን ልሆን ነው ብለሽ ነው?..... ለመሆኑ ዶላር ስንት ገባ ?»*

እናት :ምንዛሪው11 ብር ደርሷል ይላሉ!»

ልጅ :*ጨምሯላ!! ለመሆኑ ባለፈው በፖስታ ቤት የላኩልሽን ፎቶዬንስ አየሽው ?*

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com



<u>እናት</u> ፡ አዎን ልጄ!! በጣም ቆንጆ ነው!! ደሞ ወፍረሀል ተሰማምቶሀል! አንተ እንዲያው ካለ እንጀራ ሌላ ነገር መብላት አትወድም ነበር፤ ለመሆኑ ምን እየበላህ ነው፤ እንዲህ የተስማማህ?

<u>ልጅ</u> ***«አይ እማዬ! እዚህም እኮ እንጀራ አለ!!...»***

<u>እናት</u> «እንዴ ጤፍ ከየት ታገኛላቹህ? »

<u>ልጅ</u> ***«አረ እዚህ እንኳን ጤፍ ሌላውም ነገር ሞልቷል !»***

<u>እናት፦</u> በጣም ይገርማል! ..እኛ ጋር ጤፍ በጣም ተወዷል፤ ጤፉ ቢገኝ እንኳን መብራት ብዙ ጊዜ ስለሚጠፋ መጋገርም ችግር እየሆነ ነው፥ ... ጭለማ ውስጥ ነው የምንኖረው፤ .... ሻማ እንኳን እንዴት ተወዷል መሰለህ? .... እንዲያው ግን መቼ ነበር እመጣለሁ ያልከኝ?

<u>ልጅ፦</u> ***ከ3 ወር በኋላ ለአመት በዓሉ እመጣለሁ!!***

<u>እናት</u> «እሰይ!፥ እሰይ ልጄ!! እንዴት ናፍቀኸኛል መሰለህ? ..... አደራህን ታዲያ ስትመጣ ሁሉ ነገር ቀርቶ ለኔና ለአክስትህ ጤፍና ሻማ ይዘህልን እንድትመጣ ?!»

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የልጅ ነገር!



ልጅ......«እማዬ !...የሰዎች ሆድ ለምን ትልቅ ይሆናል?»
እናት......«ሲያረግዙ ነዋ ልጄ!»
ልጅ.......«አርግዘውስ ምን ይሆናሉ?»
እናት.....«በዘጠኝ ወራቸው ልጅ ይወልዳሉ!»

ልጅ..... «እንዴ!....ታድያ የአባዬ ሆድ ትልቅ ነው። እስከ ዛሬ መቼ ልጅ ወልዶ ያውቃል?»

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

እግአዚና ፍቅር

አንድ የአግአዚ ጦር ባልደረባ በጥበቃ ላይ ሳለ አንዲት ልጅ ቤተ ክርስቲያን ስትሳለም አይቶ ይወድና ለብጤ ጓደኛው *«ቧ...! አታ... ! የሆነች ልጅ እኮ በጣም ወደድኩ...?»*ሲል ያጫውተዋል።

ጓደኛውም *«ቆይ ነገ ጠዋት ታሳየኛለህ"»* ይለውና በነጋታው ማለዳ ላይ ተነስተው ቤተ ክርስቲያን ያመራሉ።

አፍቃሪው የአጋዚ ጦር ባልደረባ ልጅቷ ነጠላ ተከናንባ ከብዙ ምእመናን መካከል ቆማ አሻግሮ ያያትና... *«ዋይ...!! አታ !..ያቻትልህ..!..ያቻትልህ..!ነጠላ ለብሳ..! ትታይሃለች?»* ይለዋል ጣቱን ልጅቷ ወደቆመችበት ስፍራ ቀስሮ..

ጓደኛው ግን ከብዙ ነጠላ ለባሽ ሴቶች መካከል እርሷን ለይቶ ማየት ይሳነውና *«የታለች..?»* ሲል ይጠይቀዋል..

«ዋይ! .... ያቺ ቀንጆየዋ! .. እንዴት አትታይህም?»

ጓደኛውም *«ምን ደማሞ ያዲሳባ ልጆች ሁሉም ቆንጆ ናቸው በምን ይለያሉ?»* ብሎ ቢለልስለት፤ ፍቅር የያዘው አግአዚ *«ቆይ ላሳይህ..!»* ይልና ያነገበውን ክላሽ አውርዶ በማቀባበል ልጅቷን ጭንቅላትዋን ይመታትና*...«አየሃት?! ...ያቺ !.... የወደቀችው!!»* ይለዋል

ጓደኛውም *«እኔ ደማሞ ይቺን ያልክ መሰሎኝ..!»* ብሎ በተራው አጠገቧ የነበረችውን ልጅ በጥይት ቀንድቦ ጣላት ይባላል።

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ቅዱስ ገብርዔል ተከተለኝ!

በሃገራችን በአብዛኛው አነስተኛ የጭነት አገልግሎት የሚሰጡት አይሱዙ መኪናዎች ናቸው። አይሱዙዎች በተለይም ከደቡብና ምስራቅ የሃገራችን ክፍሎች ጫትና ሌሎችም ነገሮችን ጭነው ከተወሰነው በላይ በሆነ ፍጥነት ወደ አዲስ አበባ ሲከንፉ በተደጋጋሚ አደጋ እያደረሱ በሰው ህይወትና በንብረት ላይ ብዙ ጉዳት በማድረስ ስለሚታወቁ ሕብረተሰቡ *«አልቃይዳ»* የሚል ስያሜ ሰጥቷቸው እንደነበር አስታውሳለሁ።

እንደሚታወቀው ደግሞ በሃገራችን በተለይም ከከተማ ውጭ አገልግሎት የሚሰጡ መኪናዎች ጀርባ ላይ አንዳንድ ፅሁፍ ማስቀመጥ የተለመደ ነገር ነው፤ ታዲያ በአንድ ወቅት ከኋላ በኩል *«ቅዱስ ገብርዔል አንተ ተከተለኝ!!»* የሚል ፅሁፍ ከኋላው ለጥፎ በጣም የሚበር አይሱዙ ያዩ ከኋላ በሌላ መኪና የሚጓዙ አባት ምን አሉ መሰላችሁ፤..... *«አይ ..... በዚህ ፍጥነትህማ ምኑን ቅዱስ ገብርዔል ተከተለህ ?!»*

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

አውቶቡስ ጠባቂዎቹ

አግአዚዎች ሰው ተሰብስቦ አንድ ቦታ ሲቆም ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ስለሚመስላቸው ደስ አይላቸውም ::

ታድያ በምርጫው ሰሞን አዲስ አበባ ውስጥ ፌርማታ ላይ አውቶቡስ በመጠበቅ ላይ ወደነበሩት ሰዎች አንድ የአግአዚ ጦር ባልደረባ እየተክለፈለፈ ይመጣና *«ተበተኑ !! ምን ልታደርጉ ነው የተሰበሰባችሁት?!»* ሲል ያፈጥባቸዋል። ሰዎቹም በፍርሃት እየተርበደበዱ *«ኣረ ባስ እየጠበቅን ነው !’»* ብለው ሲመልሱለት። አግአዚው የመሳሪያውን አፈሙዝ ወደነርሱ አዙሮ *«’ተበተን !! ነው ያልኩህ! ለመጠበቅ አንድ ሰው ይበቃል! ሌሎቻችሁ ከዚህ ቦታ ዞር በሉ!»* በማለት አንድ ሰው ብቻ ሲቀር ሌሎቹን አባረራቸው ::

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የመንግስቱ ኃ/ማርያምና የመለስ ዜናዊ ሚስቶች የስልክ ወግ

(ወ/ሮ ውባንቺ ቢሻውና ወ/ሮ አዜብ መስፍን (ጎላ)

ውባንቺ ...«ሃሎ!.ወይዘሮ አዜብ እንደምን አለሽ?»

የመለስ ዜናዊ ሚስት ተጋዳላይ አዜብ ጎላ ጫካ ውስጥ ሳለች

አዜብ ...«ደሃን !ደሃን !ማን ልበል?....»

ውባንቺ.....«ከሃራሬ ነው የምደውለው። የቀድሞው የኢሰፓ ዋና ጸሃፊ፤ የአብዮታዊ ጦር ጠቅላይ አዛዥ፤ የሚንስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢ፤ የጓድ ሊቀመንበር ....»

አዜብ.......«ዋይ!!!....ግደፊ በቃ ተረዳሁሽ። ቀዳሚ ጠርናፊው ምሽት ነን አትይኝም?»

ውባንች......«አዎን ነኝ!..»

አዜብ........«ሃራይ! ምን ፈለግሽ?..»

ውባንቺ.....«እንጦጦ ማርያም ስለት ስላለብኝ ልመጣ አስቤ ነበር ባልሽን ታስፈቅጅልኛለሽ?»

አዜብ.......«ሃራይ!..ቆይ አንደ ልጠይቀው......... (ተነስታ መለስን ካነጋገረች በኋላ ትመጣለች........ "ትሰምኛለሽ ?... እሑ..ስለትሽ ምንድን ነው? ልወቀው ብሏል»

ውባንቺ.....«ስለቴ አንድ ኪሎ ወርቅ ነው»

አዜብ......«ደሀና !መቀሌ ማርያም ነው የምታስገቢው እሺ?»

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

<u>ውባንቺ</u>....*«እንዴ!! እኔ እኮ የተሳልኩት ለእንጠጠ ማርያም ነው ?!»*

<u>አዜብ</u>.......«ዋይ..!ጠርናፊዋ የመቀሌ ማርያም ነች ብዬሻለሁ.....»

<u>ውባንቺ</u>.....*«ምነው እቴ !! አሁንስ አበዛችሁት!!! ደግሞ እመቤቴ ማርያምን ልትከፋፍሉ ፈለጋችሁ? የናንተን ጉድ ቁልቢ ገብርኤል ያሳየኛል ቆይ!..»*

<u>አዜብ</u>.......«ዋይ !..ምን የማይረዳት ናት ይቺ?! አለ ጠርናፊው!............. ትሰሚኛለሽ ? .....ካሁን በሁዋላ አለ ክልልሽ አትሳይ እሺ? .»

<u>ውባንቺ</u>.....*«እሞታታለሁ እንጅ ስለቴን ለእናንተ አልሰጥም.... »*

<u>አዜብ</u> ....«ሙቺ !..ዋይ..! እኔ ታዲያ ምን-አገባኝ .!... ታውቂያለሽ?..እንኳን አንቺ ህወሃትም ሞቷል!..»

<u>ውባንቺ</u>....«ጊዜው ደርሷል ጠብቂ! ግድ የለም ቆይ...!! »...

<u>አዜብ</u>.......«በይ ባክሽ አንቺ ስራ ፍትነሽ ! ካንቺ ጋር ስዛረብ ወጤ እንዳይጎረናና እንዳታስገመግሚኝ!»

<u>ውባንቺ</u>.....«ደግሞ በየትኛው ሙያሽ ነው ወጥ የምትሰሪው ባክሽ?!! ቂቂቂቂ.....»

<u>አዜብ</u>.......«...ሉቅ-በይ ! አንቺ ትምክተኛ! የትምክተኛ ምሽት !..»

<u>ውባንቺ</u>......«አይ !..ሙያውን እንኳን ለእኛ ተይው ! አንቺ ዝም ብለሽ እንደለመድሽ ስኳር ሽን ቃሚ! በርግጥ በረሃ ሳለሽ ምድብ ስራሽ ገንፎ መስሪያ ጎላ መሸከም እንደሆነና በዚህም የተነሳ <አዜብ ጎላ> እንደተባልሽ የዛሬን አያርገውና ያኔ አብርሃም ያየህም አጫውቶኝ ነበር። ምናልባት አሁን

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ሙያተምረሽ ካልሆነ...?»

አዜብ........«ዋይ..! የበረሃውን ነው የምትዛረቢ? .... አሽርተ ሽሙንተ ዓመት እኮ አለፈው? አልሰማሽም እንዴ? አብርሃምም አሁን የኛ ደጋፊ ሆኗል እኮ?

ውባንቺ......«እርሱን አውቃለሁ ባክሽ!! ቢሆንም በብአዴን ማእከላዊ ኮሚቴ ካልተረዳሽ ብቻሽን ወጥ መስራት እንደማትችይ የታወቀ ነው። ለመሆኑ የቤተ-መንግስቱ በርሜሎች ጠጅ ተጥሎባቸው ያውቃሉ?»

አዜብ.....«ላ..! እኔን ይወዳል ወዲ ጎላ..! ምን አልሽ አንቺ?! ደግሞ የትምክተኛ መጠጥ ልጠጣ ፈለግሽ? ደፋር ነሽ በጣም!..»

ውባንቺ.....«ምን-በወጣሽ ?! እንደለመድሽው በፎሃ በሶሽን በጥብጭና ጠጭ እንጂ! መቼስ ታየኝ ያ የጠጅ በርሜል የዱቀት እቃ መስሎ..!

አዜብ.......«አንቺ ምላሳም ነሽ....ዋይ.!..አሽርተ ሽሙንተ አመት አለፈኝ አልኩሽ እኮ ከበረሃ ከወጣሁ..! አልተረዳሽም..? ዋይ.! የሽራተንና የሂልተንን አምባሻና ኬክ ማን ሊበላው፤ እኔ በሶ እጠጣለሁ?»

ውባንቺ....«አምባሻም የኬኮች ጠርናፊ ሆኖ ሽራተንና ሂልተን ገባ እንዴ? ..»

አዜብ.......«ዋይ..! ይቺ ሴት ምላስ አሳት..!በቃ ተሰፋ ስትቆርጭ ስድብ አበዛሽ? ቁም ነገር ተዛረቢ ..ዋይ!!»

ውባንቺ...እሺ !..እሺ...! ለመሆኑ ለኢትዮጵያ ህዝብ ምን አስባችሁለታል?»

አዜብ...... «አሁን ደህና አልሽ...አልሰማሽም እንዴ? የአክሱምን ሃውልት ከጣሊያን ሃገር አስመጣንለት እኮ?»

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

<u>ውባንቺ...</u>«ስም ቻለሁ..ባክሽ!....ዳቦ ለጠየቀው ህዝብ ድንጋይ ብታስመጡለት አይበላው ነገር !! ደግሞም በወያኔ ሳይሆን ነፍሳቸውን ይማረውና ፊታውራሪ አመዴ ለማ እና ፕ/ር ሪቻርድ ፓንክረስት ለዘመናት ባደረጉት ትግል ነው የተመለሰው።.....»

<u>አዜብ</u>.....*«አንቺ ግደሬ..! ዋይ..! የሶስት ሽህ አመት ታሪክ ዋይ ..!...... ድንጋይማ አትበይ...»*

<u>ውባንቺ</u>...«አለቃ እንባቆም ያሉትን ልንገርሽ

«የብዙ ሺህ አመት መሆኑ ተረስቶ

ወያኔ ቀጠረው በመቶ በመቶ»

<u>አዜብ.... </u>*«ጠባቦች ናቸው በመቶ የቆጠሩት ..... አሁን ጠባብ የለም.....!ተረዳሽ?..»*

<u>ውባንቺ... </u>«በመጀመርያ ኢትዮጵያ ያላት የመቶ አመት ታሪክ ነው ያለው እኮ ያንቺ ባል ነው?»

<u>አዜብ</u>.....«*ያኔ እንደዚያ ያለው ኢሳያስ አሳስቶት ነው እኮ? እርሱንም ቢሆን የተማሉ ጊዜ በማምገማ ሂሱን አውርዶአል...»*

<u>ውባንቺ</u> .... «እሺ! ሌላስ ለህዝቡ ምን አስባችሁለታል?

<u>አዜብ...</u>«*ሌላ ከፈለግሽ ሪፖርተር ጋዜጣ አንብቢ..»*

<u>ውባንቺ</u>...«እኔ እንኳን የምወደው ፤ ኢትኦጵን፤ ምኒልክን፤ መብረቅንና ጦቢያን ጋዜጣ ነው»

<u>አዜብ</u>.....*«እነርሱማ ጸረ-ሕዝብ ናቸው አታንቢ»*

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ውባንቺ.....«ይሄ ሁሉ ወርቁን እንዳስገባ ነው..? ሲያምርሽ ይቅር እንጅ መቀሌ መጥቼ አልሰጥሽ ነገር...?»

አዜብ......«እኔ ወደ መሰፍን ነኝ ያንቺ አንድ ኪሎ ወርቅ ሲያምረኝ የምቀረው? አሁን አሁን ተውኩት እንጅ ከባሌ ጋር ወደ ውጭ ስንሄድ እና እንግዳ ስቀበል የማደርገው ወርቅ ብቻ ከኪሎ ይበልጣል። በቴሌቭዥን እንኳን አይተሽኝ አታውቂም?»

ውባንቺ.....« የረሳሁትን ነገር አመጣሽ..! አንቺ አስዳቢ አኮነሽ?!! .. ኣረ ለመሆኑ ያንድ የሃገር መሪ ሚስት እንዴት እንደ ተራ ሰው በወርቅ ተሽቀጥቅጣ እንግዳ ፊት ትቀርባለች? ...እኔማ ሌላም ጉድሽን ሰምቸልሻለሁ! .....»

አዜብ........"ሉቅ በይ!!...አንቺ ስለሌለሽ ቅናት ነው እንዲህ ሚያደርግሽ። ዋይ..! እኔማ ከፈለግኩ ውሻየንም በወርቅ ማስር እችላለሁ። ... እድሜ ለአላሙዲ ! አደላ ጨው መስለሽ የሚወጣው.? ይልቅ ምንድነው የሰማሽው...?»

ውባንቺ.......«የሰው ቀላል!...እንደው እነ እቴጌ ጣይቱን ያፈራች ሃገር እንዳንቺ አይነት ግልቱ ሴት ታፍራ?»

አዜብ........«ደግሞ ከዚያች ትምክተኛና ነፍጠኛ ጣይቱ ጋር ልታወዳድሪኝ ፈለግሽ?...ይልቁንስ ይህን ተይና ያልሽውን ንገሪኝ?»

ውባንቺ.....«የጅቡቲ ቀዳማይ እመቤት የለበሰችውን ልብስ እንዴት አስወልቀሽ ትለብሻለሽ? አንቺ ከፈለግሽ ገዝተሽ አትለብሽም?»

አዜብ.......«ዋይ..! ደግሞ ይሄን ማን ነገረሽ? ይሄ መለስ እኮ የደርግ ሹሞችን መልሶ እየሾመ ጉድ ሳንሆን አንቀርም! እኔ እኮ ሰጭኝ አላልኩዋትም.ቀሚሱን ለብሳው ሳየው በጣም ስለወደድኩ ከየትና ስንት እንደገዛችው ስጠይቃት ወድያው ሌላ አስመጥታ ሰጠችኝ፣ እንጅ የለበሰችው አይደለም አውልቃ የሰጠችኝ...!»

ውባንቺ....«አሳፋሪ..! እኔ...ይህን ሰማሁ እንጅ አንቺ ይሄኔ የአልበሽርንም ሚስት ፓንት አስወልቀሽ ለብሰሽ ይሆናል..!

አዜብ......«ዋይ..!በይ ተይኝ! ...አወይ ምላስ እሳት!..»

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

<u>ውባንቺ</u>…«ኣረ ወዲያልኝ እቴ!! …. ጓድ ሊቀ መንበር ከእንቅልፋቸው የሚነሱበት ሰአት ስለደረሰ ነው እንጂ ያንች ጉድ መች ተዘርዝሮ ያልቃል?..በይ ደህና ሁኝ እቴ!»

<u>አዜብ</u>…….*«ወይ ጉድ!! ባልሽ እስካሁን ይተኛል? … ጠቅላይ ሚኒስትሩ እኮ የጀበና ቅመው ፤ አሁን ሰሞኑን የሚወጣ ሕግ ፅፈው ጨርሰዋል? ይልቁንስ በርጫውን ልጨምርላቸው እቴ!! መችስ እርሳቸው ዱአ ሳያደርጉ ቢሮ መግባት አይወዱ!!….. በይ ሰላም ዋይ ጓዴት ውባንቺ….!»*

(ይህ ፅሁፍ የተወሰደው ከቋጠሮ ድረ-ገጽ ሲሆን፤ አንዳንድ እውነታዎች ታክሎበት እንደገና የተዘጋጀ መሆኑን ማስታወስ እሻለሁ) ………………….//…………………

የቀብር ፍቃድ

ሁል ጊዜ ምክኒያት እየፈጠረ ከስራ የሚቀር አንድ ሰራተኛ አርፍዶ ወደስራው ሲገባ አለቃው ይጠራውና_«ከሞት በኋላ ህይወት እንዳለ ዛሬ ባንተ አመንኩኝ» ይለዋል

<u>ሰራተኛ</u> …….. «እንዴት ጌታዬ?»

<u>አለቃ</u>……. «ከትላንት ወዲያ ሞታለች ብለህ ፍቃድ የጠየክባት አክስትህ ጠዋት ቢሮ ደውላ ፈልጋህ ነበር፡፡»

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ዳኛ እና ተከሳሽ

ዳኛ..... «.ጠርሙስ ወርውረህ በሚስትህ ራስ ላይ ሰብረሃል ተብለህ ተከሰሃል። በዚህ ጉዳይ ለፍርድ ቤቱ የምትገልጸው ነገር አለ? »

ተከሳሽ.....«ሳላስበው የተፈጸመ ድንገተኛ ነገር ነው ክቡር ሆይ»

ዳኛ.........«ሳላስበው የሆነ ድርጊት ነው ስትል ምን ለማለት ፈልገህ ነው?»

ተከሳሽ......«ማለት ... በወቅቱ ጠርሙሱን ስወረውረው ይሰበራል ብዬ አልገመትኩም ነበር»

................//..................

ፍቅርና ገንዘብ

ሴት ልጁ በመረጠችው እጮኛ ያልተደሰተ አባት ነገሩ ሁል ጊዜ ቢከነንክነው፤ አንድ ቀን ተነስቶ *«ልጄ! የምነግርሽን ነገር ስሚ፤ ይህን ልጅ በምንም አይነት መንገድ ማግባት አይኖርብሽም። እንዴ!...ምን ነካሽ?....ምንም የሌለው ምላጩ ደሃ! የደሃ ልጅ እኮነው?! ....እንዴ ! ምን ማለትሽ ነው?! ሌላው ቀርቶ በወር 100 ብር እንኳን አያገኝም እኮ!...»* ሲል ሊመክራት ይሞክራል።

የአባትዋ አነጋገር ያልተዋጠላት ልጃገረድም ቀበል አድርጋ..«አይ አባዬ!..አንተ አላወቅክም ለካ?...ፍቅር ሲይዝ እኮ ወሩ ሳይታወቅ ነው የሚያልፈው? !» ስትል አባትዋን ተማጸነች ይባላል።

................//..................

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የመረረው የአበሻ ልጅ



አንድ ኑሮ በዚህ ቢለው፤ በዚያ፤ አልቃና ያለው ያበሻ ልጅ መጨረሻ ላይ ምርር ይለውና ህይወቱን ለማጥፋት ቆርጠ ይነሳል። ይህንንም ሃሳቡን በወቅቱ አለኝ ወደሚላት የቅርብ ጓደኛው ጋር በመሄድ *«አሁንስ ሁሉም ነገር በጣም ስለመረረኝ በቃ ራሴን ለማጥፋት አስቤአለሁ»* በማለት ያማክራታል።

በዚህ ጊዜ እርሷም *«ሃሳብህ ጥሩ ነው፤ ሆኖም ማን ይህን ነገር ለእኔ እንደነገርከ ለሌላ ሰው እንዳትናገር! እንዲህ አይነት ነገር ፈጽሞ ሌላ ሰው መስማት የለበትም !!»* ስትል በጥብቅ ታስጠነቅቀዋለች።

ሰውዬው ይህ የጓደኛው ማስጠንቀቂያ ግራ ቢያጋባውም *«ማን ለምንድነው ሰው እንዳይሰማ ያልሽኝ? ሰው ምን የሚያመጣው ነገር ይኖራል? እኔ ቆርጬ ከሞትኩ በኋላ የሚከተለኝ ነገር አለ እንዴ?»* ብሎ ቢጠይቃት

«አይ! ለዚያ እንኳን አይደለም!.....ምናልባት ለሰው ስትናገር መቼስ አበሻ ምቀኛ ነውና ሃሳብህን ያስቀይርሃል ብዬ ፈርቼልህ ነው።» ስትል መለሰችለት ይባላል።

......................................//..................................

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

አሜሪካና ሰዓት አቆጣጠር



መምህሩ በክፍል ውስጥ በአለማችን ላይ ስላለው የሰዓት አቆጣጠር ልዩነት ለተማሪዎቻቸው አስረድተው ሲጨርሱ ለተማሪዎቻቸው ጥያቄ ያቀርባሉ።

መምሕር፤- ***«.... የኢትዮጵያና የአሜሪካ የሰዓት አቆጣጠር ብዙ ልዩነት አለው። የኛ ሰዓት ከአሜሪካ በጣም የተደመ ነው። የእኛ አገር ከምሽቱ 12 ሰዓት ሲሆን እዚያ ገና ከማለዳው 12 ሰዓት ነው። ይህ ከምን የመጣ ይመስላችኋል?»***

ተማሪ፡- ኢትዮጵያ የ3 ሺህ ዓመት ዕድሜ ሲኖራት፤ ክሎስቶፎር ኮሎምቦስ አሜሪካን ያገኛት ግን ከኛ በጣም ዘግይታ በመሆኑ ነው። ❚

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የባል ኑዛዜ

ባል ጣዕረ-ሞት ይዞት ሊሞት እያጣጣረ ሳለ ሚስቱን ያስጠራና *«እንግዲህ እኔ መሞቴ ነው፤ አንቺ ግን ያለ ባል መቅረት የለብሽም፤ እንዲያውም ያንን ተፈራን አግቢ»* ይላታል።

በዚህም የተናደደችው ሚስት *«አንተን ይማርልኝ እንጂ እኔ አሁን ስለ ባል አላስብም፤ ደግሞ ባገባስ እንዴት ያንተን ዋነኛ ጠላት ተፈራን አግቢ ትለኛለህ?»* ስትል ትጠይቀዋለች።

በዚህ ጊዜ ጣር የያዘርው ባል እያቃሰተ መለስ አድርጎ *«አንቺ ደግሞ አይገባሽም እንዴ?! ጠላቴ መሆኑንማ መች አጣሁት? ልክ እንደ እኔ እንገብግበሽ እንድትገድይልኝ ነው እንጂ!»* አላት ይባላል።

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

አባ ጳውሎስና ልደታ

በጠቅላይ ቤተ ክህነትና በአዲስ አበባዋ የማሕደረ ስብኃት ቅድስት ልደታ ለማሪያም ቤተክርስትያን መካከል በተፈጠረው አለመግባባት ከ 1992-1995 ድረስ በርካታ የቤተ ክርስቲያኗ ካህናትና ምዕመናን በመንግስት ታጣቂ ሃይሎች በተደጋጋሚ ታስረዋል፤ ተደብድበዋል፤ እንዲሁም የሰው ህይወት ሁሉ ማለፉ ይታወሳል።

በመጨረሻም በአባ ጳውሎስ የልደታ ተቃዋሚዎቻቸውን በወንዝ ልጆቻቸው ረዳትነት በታንክ ሁሉ የታጀበ በርካታ ዘመናዊ መሳርያ የታጠቀ ጦር በማዝመት የበርካቶችን ደም አስፈስሠው በሃይል የቤተክርስትያኗን መንበር ጨብጠዋል። ታድያ በአንድ ወቅት አባ ጳውሎስ አዲስ አበባ ውስጥ

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የሚገኝ አንድ ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ምዕመናንን መስቀል እያሳለሙ ጥያቄ ይጠይቃሉ።

<u>አባ ጳውሎስ</u>.....*«አንተ ከየት ነውየመጣኸው?»*

<u>ተሳላሚ</u>..........«ከቀጨኔ መድሃኔአለም»

<u>አባ ጳውሎስ</u>.......*«እግዚአብሔር ይፍታህ! አንተስ ሌላኛው ከየት ነው የመጣኸው?»*

<u>ተሳላሚ</u>..........« ከተክለ-ሃይማኖት፡»

<u>አባ ጳውሎስ</u>......*«በል እግዚአብሔር ይፍታህ፡! ሌላም አለ ለካ? .... ደግሞ አንተስ ከየት ነው የመጣኸው ?»*

<u>ተሳላሚ</u>............«ከልደታ !»

<u>አባ ጳውሎስ</u>...*«ውይ !! ውይ!! ....በል ያንተንስ እኔ አያገባኝም፤ እዚያው ፌደራል ፖሊስ ይፍታህ !»*

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

እስኪርቢቶ የዋጠው ልጅ

እናት በቅርቧ ወዳለው ሆስፒታል ድንገተኛ ክፍል ስልክ ትደውላለች ::

<u>ነርስ</u> *«ሀሎ !! ምን እንርዳዎት?»..*

<u>እናት</u> *«ኣረ በነፍስ ድረሱልኝ !! ልጄ ድፍኑን እስኪርቢቶዬን ዋጠው እኮ?»*

<u>ነርስ</u> *«እሺ አሁኑኑ እርዳታ የሚሰጥ አምቡላንስ እንልክሎታለን»*

<u>እናት</u> *«አምቡላሱ እስኪመጣ እኔ ምን ላድርግ ታዲያ»*

<u>ነርስ</u> *«እስከዚያው በእርሳስ ይፃፉ!!»*

ቦክሰኛና ጋዜጠኛ

<u>ጋዜጠኛ</u>*....«የነገው ተጋጣሚህ «ሪንግ ውስጥ በአንድ ምት ዘርሬ እገድለዋለሁ!» እያለ እየዛተብህ ነው፤ ለዚህ ምን ምላሽ ይኖርሃል?»*

<u>ቦክሰኛ</u>*.....«እርሱን እንኳን ተውው! ይህንን እኔ አስቀድሜ ለፖሊስ አመልክቻለሁ!»*

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ተወደድኩ ባይ!!

<u>ልጃገረድ</u> ; *«ታቃለህ! .... አንተን ባየሁ ቁጥር አንድ ትልቅ ሰው ትውስ ይለኛል »*

<u>ተወድጃለሁ ባይ</u> ;*«ውይ ታድዬ!! ማነው ግን የኔ ቆንጆ?»*

<u>ልጃገረድ...</u>*«ሳይንቲስቱ ቻርለስ ዳርዊን»*

<u>ተወድጃለሁ ባይ</u> ; *እንዴ?! እኔ ክርሱ ጋር በመልክ ሆነ በቁመና አልመሳሰል! በችሎታ አልመጣጠን! .... እንዴት ሆኖ ነው እሱ ትዝ የሚልሽ የኔ ሽጋ?»*

<u>ልጃገረድ</u> ; *«መጀመሪያ ሰው ከዝንጀሮ ነው የመጣው ያለው እሱ አልነበር?!»*

ምግብ ቤት

ሁለት ጓደኛሞች ምግብ ቤት ይገባሉ:: አስተናጋጇም የሚታዘዙትን ጠይቆ አንድ የበግ ቀይና አንድ አልጫ ወጥ ያመጣላቸዋል። ታዲያ የአልጫው ወጥ ስጋ ብጥቅጥቅ ያለበት አንደኛው እንግዳ አስተናጋጇን ጠርቶ *«ስማ እንጂ አንተ!»* ይለዋል በቁጣ!

<u>አስተናጋጅ</u> *«አቤት ምን ጎደለ ጌታዬ?»*

«ለመሆኑ በጓ በቢላዋ ነው የታረደችው ወይስ በፈንጂ ነው የተመታችው?!

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የባልና ሚስት ነገር



ሽማግሌ አያትና ልጅ አያወጉ ሳለ ልጅ በመሃል እንዲህ ሲል ይጠይቃቸዋል።

«አባባ !.... በድሮ ግዜ ባልና ሚስት እስኪጋቡ ድረስ አይተዋወቁም የሚባለው እውነት ነው?»

<u>አያት</u> <<አዎን ልጄ! ... ግን እኮ አሁንም ቢሆን እንደዚያው ነው፤ ... ብዙዎቹ ከተጋቡ በሁዋላ ነው ማንነታቸውን የሚተዋወቁት>>

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

መቶ ብርና የወያኔ ጠላትነት

ወያኔዎች አዲስ አበባ የገቡ ሰሞን በየመንገዱ ደስ ያላቸውን ሰው እያስቆሙ መታወቂያ ይጠይቁ ነበር። ታዲያ መታወቂያ የሌለው ሰው ካጋጠማቸው *«ሊሰፓ፤ የደርግ ርዝራዥ፤ ወታደር፤»* ወዘተ ....እያሉ ይደበድቡ፤ ያስሩ፤ ደስ ካላቸውም ይገድሉ ነበር።

.ታዲያ ድንገት አንድ ቀን መንገድ ዘግተው ሲፈትሹና መታወቂያ ሲጠይቁ ሰውየው ባጋጣሚ መታወቂያ አልያዘም ነበርና የሚያደርገው ቢያጣ አንድ የኢትዬጱያ ብር ኖጭ የፕላስቲክ የኪስ ቦርሳው ውስጥ እንደታጠፈ *«ይሄው መታወቂዬ»* ብሎ በድፍረት ያሳየዋል።

ወያኔውም ቀበል አድርጎ ካየው በኋላ *«እታ!! ስትስቅ እንዴት ታምራለህ?»*ብሎት ይመልስለታል። ድንገት የሚቀጥለው ተጠያቂም መታወቂያ ያልያዙ በእድሜአቸው ትልቅ ሰውዬ ነበሩና ይህንን በማየት 100 ብር ቦርሳቸው ውስጥ አድርገው ሲያሳዩት

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የወያኔው ጭፍራ መቶ ብሩ ላይ ያለውን የአርበኛ ምስል አይቶ በንዴት *«እንዴ !! ዋናው የምትፈለገው ነፍጠኛ አንተ አይደለህም እንዴ? .... በል ጠጠው በል!!»* በማለት እያገላበጠ ወሰዳቸው ይባላል። በነገራችን ላይ ወያኔ በደርግ ዘመን የነበረውን የኢትዮጵያ ብር ቀለሙን በተወሰነ መልኩ ቀይሮ አሁንም እንዲያገለግል ሲያደርገው መቶ ብሩ ላይ የነበረውን የአባት አርበኛ ምስል ግን ሙሉ ለሙሉ አንስቶታል።

.........................\\\\.........................

የነጋዴ ልጅ

የአንድ በአገር የታወቀ ነጋዴ ልጅ አንድ ቀን አባቱን *«አባባ! .. አምስት መቶ ብር አበድረኝ?»* ሲል ይጠይቀዋል።

አባት፤- «ለምን ፈለግከው?»

ልጅ፤- *«አንድ እቃ በአምስት መቶ ብር አገኘሁ፤ እቃው ሰባት መቶ ብር የሚያወጣ ነው። ሲሸጥ ገንዘብህን መልሼ ትርፉን እኩል እንካፈላለን።»*

አባት፤- «ግድ የለም! ... አሁን ንግዱ እንደተሳካ እንቁጠረውና አንተም ማትረፍ የፈለግኸው አንድ መቶ ብር ይኸውልህ፤ እኔም አራት መቶ ብሬን ላትርፍ፤» አለው።

. ...\\\\.........................

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የመጠጥ፡ነገር



አንድ ሰውዬ ወደ ባቡር ጣቢያ ጠዋት ይሄድና *«ትናንት ማታ ባቡር ውስጥ አንድ ጠርሙስ ውስኪ ረስቼ ነበር፤...... ምናልባት ሰዎች አግኝተውት ጠፍቶ የተገኘ እቃ የሚሰበሰብበት ክፍል ውስጥ አስቀምጠውልኝ ይሆን ?»* ሲል ይጠይቃል።

የባቡር ጣቢያው ሰራተኛም «*እዩ !! ... ጠርሙሱ ሳይሆን፤ ጠርሙሱን ያገኘው ሰውየ ወድቆ ሳይገኝ አይቀርም»* ሲል መለሰለት።

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የመዶሻ ሰዓት

አንድ ቀን አንዱ ሰካራም ከመጠጥ ቤት መልስ ጓደኛውን «*ቤቴን ገብተህ ማየት አለብህ በማለት*» ይዞት በመግባት እያዞረ ክፍሎቹንና እቃዎቹን ሁሉ ያስጎበኘው ጀመር።: ታድያ እንግዳው የሰካራሙ አልጋ አጠገብ አንድ ትልቅ መዶሻ ተቀምጦ ያይና ብድግ አድርጎት *«ይህ ደግሞ ምንድነው ?»*ሲል ይጠይቀዋል።

"ሰዓት ነው !...ተናጋሪ ሰዓት !" ሰካራሙ መልስ ሰጠ

መዶሻውን አገላብጦ ቢያየውም ምንም ሰዓት የሚመስል ነገር ያጣበት እንግዳም *«ትቀልዳለህ እንዴ? »* ይለዋል ነካ አድርጎት ይሆን እንዴ በማለት በውስጡ እየተጠራጠረ። ይሔኔ ሰካራሙ *"ቆይማ እንዴት እንደሚሰራ ላሳይህ "* ብሎ ከእንግዳው ላይ መዶሻውን ተቀብሎት ግድግዳውን ይደበድብበት ጀመር::

ይሄኔ ከጎረቤት *«ኤጭ ! ይሔ ሰካራም ደግሞ ተነሳበት!! መጣ መሰል! ....አሁን እስኪ ምን ሆንኩ ብሎ ነው ከለሊቱ ሰምንት ሰዓት ከሩብ ግድግዳዬን የሚደበድበው !!» የሚል ድምጽ ተሰማ።»*

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የአውቶቡሱ ሾፌር !

ወያኔዎች አዲስ አበባ እንደገቡ አንዱ ወደ ደብረ-ዘይት የሚሄድ አውቶቢስ ሊሳፈር ወደ ለገሃር መኪና ተራ ይሄዳል። ታዲያ አጋጣሚ ወደ ደብረ-ዘይት የሚሄደው አውቶቡስ ሞልቶ ያለው ክፍት ቦታ የሾፌሩ መቀመጫ ብቻ ነበርና ዘሎ ገብቶ እዚያ ላይ ጉብ ይላል።

አውቶቡሱ የሚነሳበት ሰዓት ደርሶ ሾፌሩ ወደ መኪናው ሊገባ በሩን ሲከፍትም ቦታው በሌላ ሰው ተይዞ ያይና በግርምት «ይቅርታ የኔ ወንድም! ይህ ቦታ እኮ የኔ መቀመጫ ነው?» ይለዋል ትህትና በተሞላበት አነጋገር።

ወያኔውም «እንዴ እኔ ቀድሜሃለሁ! አሁን ከኋላዩ መጥተህ የኔ ቦታ ነው ስትል ትንሽ አታፍርም?» ሲለው ሾፌሩ ሰውዬው ስለመኪና ምንም እንደማያውቅ በመረዳት «እኔ እኮ የመኪናው ሾፌር ነኝ! መኪናውን ደግሞ የምነዳው እዚህ አንተ የተቀመጥክበት ወንበር ላይ ሆኜ ነው» በማለት ሊያስረዳው ሞከረ።

ሆኖም ወያኔው በድርቅናው በመፅናት « አንተ እዚህ ቦታ እንቁላል ጥለህበታል እንዴ?!! ... ከፈለግክ ወደኋላ ቦታ ፈልገህ ንዳ!!» ሲል መለሰለት ይባላል።

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ሰብዓዊ-መብት

ወያኔ የ1997ቱን ምርጫ ተከትሎ በህዝባችን ላይ ያደረሰውን ጭፍጨፋ በተመለከተ የህዝብ አስተያየት በመሰብሰብ ላይ የነበረ አንድ የውጭ ሃገር ጋዜጠኛ ወደ አንድ መንፈሳዊ አባት ዘንድ በመሄድ «የኢህአዴግ መንግስት በህዝቡ ላይ የወሰደው የጭካኔ እርምጃ አግባብ ነው ወይንስ አይደለም?» ሲል ይጠይቃቸዋል።

በዚህ ጊዜ መንግስትን ለመወንጀል የሚከተላቸውን ጣጣ የፈሩት፤ ግድያውንም ለመካድ ምክንያት ያላገኙት አባት ከህዝብም ሆነ ከመንግስት ላለመጣላት አስበው ምን አሉ መሰላችሁ.... «አዎን!! ...አግባብ ነውም፤ አይደለምም ለማለት በጣም ይከብዳል።...ነገር ግን መንግስት አመጽ አድራጊዎቹን ሰብአዊ መብታቸውን ጠብቆ ገድሎአቸዋል»

(ከኢትኦጵ)

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በግፍ ሲገደሉና ሰብዓዊ መብታቸው ያለአግባብ እየተጣሰ ለእስርና ለእንግልት ሲዳረጉ እያየን እንዳላየን፤ እየሰማን እንዳልሰማን፤ ዝም ማለት በዚሁ አስኮናኝ ተግባሩ አለም እያወዛው የሚገኘውን አረመኔውን ስርዓት «አይዞህ በርታ!» እንደማለት ይቆጠራል!!

ጸጋዬ ገ/መድህን (ደብተራው) ኢሕአ
በ1991 ጎንደር ውስጥ በወያኔ ተይዞ
ላለፉት 18 ዓመታት የት እንደደረሰ
እንኳን የማይታወቅ

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ
ከታሕሳስ
20/2001 ዓ.ም
(Dec.29/2008
ጀምሮ በእስር ላይ

አንድዬ ልጇ ሕፃን ሃሌ ሚደቅሳ

«ለሕዝቤ ለድርጅቴ በውጭም ሆነ በአገር ውስጥ ያስተማርኩት ሰላማዊ እምቢተኝነት ነው። ጠመንጃ ሳንይዝ ለውጥ እናመጣለን ብዬ አስተምሬያለሁ። እንግዲህ ቃሌን መጠበቅ አለብኝ። አሜሪካ መጥቼ የነበረ ጊዜ መቅረት እችል ነበር። አውሮፓ የነበርኩኝ ጊዜ መቅረት እችል ነበር። ለኔም ለትንሿ የቤት ልጂም በሥጋ የሚመችን ሁኔታ መፍጠር እችል ነበር። ነገር ግን አብረውኝ ተምረው ሥራ ያጡ ጓደኞቼስ ? በረሃብ የተጎዱ ከቻሉም በቀን አንደ ብቻ የሚመገቡ ወገኖቼስ ? ከዚህ በፊት እንድፈታ ጠዋትና ማታ ሲጸልይልኝና ሲጾምልኝ የነበረውን ሕዝቤን ጥዬ እንዴት አድርጌ እኖራለሁ? ሁላችንም ጥለን ከሄድን ኢትዮጵያንስ ማን ያድናታል ? በአገሪቱ በሙሉ ለነጻነት ለኢትዮጵያ አንድነት ለዲሞክራሲ የፈሰሰው ደም ገና ሳይደርቅ እንዴት የነሹበሬ ደላሎችን የሕይወት መስዋዕትነት እረሳለሁ? ለልጄስ የማክዶናልድ ቺክን ናጌትና ዲዝኒን ከምሰጣት የአገር ክብርን ኢትዮጵያዊነትን በራሴ መተማመንን ባወርሳት ነው የምመርጠው»

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com